## ለኮሌራ ወረርሽኝና ሌሎች የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች እየተሰጠ ያለውን የጤና ምላሽ አስመልክቶ የተዘጋጀ ሳምንታዊ መግለጫ

- ቺኩንጉኒያ
  - የቺኩንጉኒያ ወረርሽኝ በሶማሌ ክልል በቆራሂ ዞን ቀብሪ ዳሃር ከተማ በጠቅላላው **203** ሰዎች ላይ ተከስቶ የነበረ ሲሆን ከክልሉ ጋር በተደረገው የተቀናጀ ፈጣን ምላሽ ፡ የትንኝ ማጥፊጣ ርጭትና ሌሎች የመከላከል ስራዎች ተገባራዊ በመደረጋቸው ወረርሽኙን መቆጣጠር የተቻለ ሲሆን ባሳለፍነው አንድ ሳምንት ምንም አይነት ተጨማሪ ታማሚ ሪፖርት አልተደረገም።
- ፖሊዮ
  - በሶማሌ ክልል በዶሎ ዞን በአከባቢው የመደበኛ ክትባት አገልግሎት ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ተከትሎ የመነጨ የፖሊዮ ቫይረስ በአንድ ሰው ላይ ተከስቷል። በተጨማሪም ከበሽተኛው ጋር ንክኪ የነበራቸው **3** ሰዎች የበሽታው ምልክት ባይታይባቸውም የሰገራ ናሙናቸው ተመርምሮ ለተመሳሳይ የፖሊዮ ቫይረስ ዝርያ የተጋለጡ መሆናቸው ተረጋግጧል። ይህንንም ተከትሎ በዶሎ ዞን ባሉ **7** ወረዳዎች ለሚገኙ ቁጥራቸው ከ**191000** በላይ ለሆኑ ከአምስት አመት በታች ህፃናት ሲሰጥ የነበረው የመጀመሪያ ዙር የክትባት ፕሮግራም በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀ ሲሆን የሁለተኛው ዙር ክትባትም ከነሃሴ ሁለት ጀምሮ የሚቀጥል ይሆናል።
- ኮሌራ
  - በአጠቃላይ በሀገራችን በኮሌራ ወረርሽኝ የተያዙ ሰዎች ቁጥር **871** ደርሷል (በኦሮሚያ ክልል **360**፣ በአዲስ አበባ **125**፣ በትግራይ ክልል **19**፣ በአፋር ክልል **131**፣ በአማራ ክልል **202**፣ በድሬዳዋ **1**ና በሶማሌ ክልል **33**) ።
  - በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ **12**፤ በአፋር **14**፤ እና በአዲስ አበባ **7** ታማሚዎች በህክምና ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ የህክምና ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ መደበኛ ህይወታቸው ተቀላቅለዋል።
  - እስካሁን በተደረገው የማረጋገጫ የላቦራቶሪ ምርመራ በአፋር ክልል **5**፣ በአዲስ አበባ ከተማ **17**፣ በኦሮሚያ ክልል **5**፣ በአማራ ክልል **2**፣ በትግራይ ክልል **2**፣ በድሬዳዋ ከተማ

አስተዳደር 1 በአጠቃላይ በ32 ናሙናዎች ላይ ውጤቱ ቪብሮ ኮሌሬ መሆኑ ተረጋግጧል።

- ወረርሽኙ በተከሰተባቸው ክልሎች በበሽታው የተያዙ ሰዎችን ለይቶ ለማከም የሚያስችሉ በአጠቃላይ 26 የማከሚያ ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን እነዚህም ፤ በአፋር ክልል 2 (በአሚባራ ወረዳ )፣ በአዲስ አበባ 4 (በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ፤ በዘውዲቱ ሆስፒታል፣ በድልፍሬ ጤና ጣቢያና አዲስ ከተማ ወረዳ 10 ጤና ጣቢያ) በኦሮሚያ 12 (በኦዳቡልቱም 1፣ በጨሮ 5 ፣ሰንዳፋ ከተማ 2፣ ገመቺስ 1 እና በሜኤሶ 3)፣ በትግራይ ክልል 1 (በመቀሌ አዲሃቂ) እንዲሁም በአማራ ክልል ስድስት ( በአበርገሌ ወረዳ 3፣ በአባይ ማዶ ባህርዳር 1 እና ጠለምት 2)፣ እና ድሬዳዋ አስተዳደር 1 ናቸው።
- በሽታው ከተቀሰቀሰ ጀምሮ ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ 17 ሰዎች ህይወት አልፏል ከነዚህም ውስጥ 14 በአማራ ክልል (6 በጤና ተቋም ውስጥ በህክምና ላይ ሳሉ ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን 8 ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ እያሉ ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል)፣ 2 በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም 1 በአፋር ክልል ናቸው።
- በኦሮሚያ ክልል እስከ አሁን ድረስ 360 ሰዎች በወረርሽኙ ተይዘው የነበረ ሲሆን በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በጭሮ ወረዳ 95 በኦዳ ቡልቱም ወረዳ 132፣ በሜኤሶ ወረዳ 41 ፣ በገመቺስ ወረዳ 13፣ ጉሜ ቦርደዴ 11 እንዲሁም በበዴሳ ከተማ 48 ፣በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰንዳፋ ከተማ 18 ሰው እንዲሁም በበራክ ወረዳ 2 ሰው ሰዎች የተያዙ ሲሆን 12 ሰዎች በለይቶ ማከሚያ ማዕከል እየታከሙ የሚገኙ ሰሆን ቀሮዎቹ ህክምና ተከታትለው ወደ መደበኛ ህይወታቸው ተመልሰዋል። እስካሁን ድረስ ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ የሁለት ሰዎች ህይወት በበሽታው ምክንያት አልፏል፤
- እስካሁን ድረስ በአዲስ አበባ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር 125 ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 7 ሰዎች በለይቶ ማከሚያ ማዕከል በህክምና ላይ ይገኛሉ።

  - በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ 26 ሰው፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ 33 ሰው ፣በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ 14 ሰው፣ በልደታ ክፍለ ከተማ 9 ሰው፤ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ 2 ሰው፣ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ 11 ሰው፣ በጉለሌ ክፍለ

ከተማ 3 ሰው፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ 4 ፣ በየካ ክፍለ ከተማ 6 ሰው፤ ሰው እንዲሁም በአራዳ ክፍለ ከተማ 13 ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል፡፡

  - በአማራ ክልል በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር በአጠቃላይ 202 የነበረ ሲሆን፣ ላለፉት 30 ቀናት አዲስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች የሉም፡፡
  - በትግራይ ክልል በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር 19 ደርሷል፡፡
  - በሶማሌ ክልል በአተት በሽታ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 33 የነበረ ሲሆን፣ ለባለፉት 38 ቀናት አዲስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች የሉም፡፡

- ባሳለፍነው ሳምንት 291,000 የኮሌራ ክትባት ለኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሃረርጌ ዞን የተላከ ሲሆን ክትባቱም በትላትናው እለት የተጀመረ ሲሆን በቀጣይ ቀናት የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡
- የኮሌራ መድሃኒቶችና ግብአቶች ለድሬዳዋና አፋር ክልል ተልኳል፡፡
- በአጠቃላይ የበሽታው ስርጭት በአዲስ አበባና በኦሮሚያ የቀነሰ ሲሆን በአፋር ክልል ግን ስርጭቱ እየጨመረ ይገኛል፡፡ የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት ወረርሽኙ በተከሰተባቸው ወረዳዎች ህብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ የአካባቢና የግል ንፅህና አጠባበቅ ስራዎች እንዲሁም ለበሽታው መስፋፋት አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎችን በመለየት ወረርሽኙን ለማቆም ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተዋረድ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- በተጨማሪም በአፋር ክልል አሚባራ ወረዳ ከ64,000 በላይ ሰዎችን ለመከተብ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተከናወነ ሲሆን የክትባት ዘመቻ በሳምንቱ መጨረሻ የሚጀመር ይሆናል፡፡
- የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተር በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሀረርጌ ዞንና በአፋር ክልል በአሚባራ ወረዳ በመገኘት ወረርሽኙ ያለበትን ሁኔታ በመስክ በመገኘት ምልከታ አድርገዋል፡፡ በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በሜኤሶ ወረዳ በመገኘት ሲሆን ከክልሉና ከዞኑ ሃላፊዎች ጋር በመሆን የክትባት ዘመቻውን በትላንትናው እለት አስጀምረዋል፡፡ በተጨማሪም ከክልሉና ከዞኑ ጋር በድጋፍ አሰጣጡ ሂደት ላይ ተወያይተዋል፡፡
- የኩፍኝ በሽታ ከየካቲት ወር ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን አሙሮ ወረዳ 316 ሰዎች እንዲሁም በአፋር ክልል በአሳይታ ፣አፋምቦ እና ዱብቲ ወረዳዎች 347 ሰዎች ተይዘው የነበረ ሲሆን በዚህ ሳምንት 34 ሰዎች በወረርሽኙ ተጠቅተው ህክምና ተደርጎላቸው ወደ ቀድሞ ህይወታቸው ተመልሰዋል፡፡ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር የክትባት ዘመቻ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በሶማሌ ክልል በኮሎጂ የተፈናቃዮች መጠለያ ካምፕ ለሚገኙ ወገኖች የስነአእምሮ ህክምና በሳይካትሪስቶች ለአንድ ወር ተሰጥቷል። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በክልሉ ስልጠና ወስደው በነበሩ ባለሙያዎች የስነ-ልቦና ድጋፍ በመሰጠት ላይ ይገኛል።

- ከዚህም በተጨማሪ በትግራይ ክልል የስነልቦና፣ የአእምሮ ጤና እና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለተፈናቀሉ ወገኖች መስጠት እንዲቻል **80** ጤና ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ የተደረገ ሲሆን በቀጣይ አገልግሎቱን መስጠት የሚጀምሩ ይሆናል።

**የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

**ሰኔ 25 / 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**